# በኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

## በሕይወት ባሉ ዘመዳሞች መካከል ስለሚደርግ የአካል ክፍሎች ንቅለ ተከላ ህክምና አሰጣጥ መመሪያ

ጥር 2007 ዓ.ም

**መግቢያ**

ከበርካታ አመታት በፊት በበለፀጉት ሀገሮች የተጀሚረው የንቅለ ተከላ ህክምና በሃገራችን ከአይን ብሌን ንቅለ ተከላ በስተቀር ሳይተገበር የቆየ ቢሆንም በአካል ክፍሎች ህመም ምክንያት ለሚሰቃዩ እና ለሞት

ለሚጸረጉ ግለሰቦች የህክምና መፍትሄ ከማስጠት አንፃር ህክምናው እንዲዳብርና በስፋት እንዲሰጥ ለሚድረግ የአሰራር መመሪያ በሚዜለጉ፤

በሃገራችን የህግ ስርዓት ንቅለ ተከላ የሚከሄደው ለንግድ አላማ ካልሆነ እና የለጋሹን ጤንነት ሁኔታ ሚይጎዳ ሜልኩ እስከተካሄደ ድረስ ንቅለ ተከላ ማካሄድ እንደሚቻል የተደነገገ በማሆኑ፤

ምንም እንኳን ህክምናው የጤና አገልግሎት አካል ማሆኑ በሃገራችን የተለያዩ ህጎች ተደንግጎ የሚገኝ እና ህጎቹም አገልግሎቱን ለማስጠት በቂ ናቸው ሊባል ቢችልም በንቅለ ተከላ ህክምና ወስጥ ሊነሱ የሚችሉ ሌሎች ጉዳዮችን ከሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም በህግ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በማኘቱ፤

በሃገራችን በአሁኑ ጊዜ ንቅለ ተከላ ለማካሄድ የሚችሉ የጤና ተቋማትን መፍጠር እንደሚቻል ከግንዛቤ በማስገባት ህክምናወን በነዚሁ የጤና ተቋማት በማስጠት ዜጎች ህክምናወን ለማግኘት ወደ ሌላ ሃገር በሜድ የሚያወጡትን ከፍተኛ ወጪ እንዲያስቀር እንዲሁም ህክምናወን ፍትሃዊ በሆነ ሜልኩ ለሁሉም ታማሚዎች ተደራሽ እንዲሆን ወጥ የአሰራር ስርዓት ለማዘርጋት፤

ከሌሎች ሃገራት ተሞክሮ የንቅለ ተከላ ህክምና አገልግሎት ለንግድ አላማ መዋሉን ለመቆጣጠር አዳጋች ሆኖ ለከፍተኛ የማህበራዊ ቀወስና የወንጀል ድርጊት የሚያጋልጥ ማሆኑን በሚዳት የሰዎች የአካል ክፍሎች ለማጋገጃና ለማትረፊያ እንዳይሆኑ ለማካላከል፤

ከንቅለ ተከላ ህክምና ጋር ተያይዞ ሊከሰቱ የሚችሉ የሰዎችን ሰብአዊ ክብርና ማስረታዊ ነፃነቶች የሚጋፉ ማኝቸወም ከስነምግባር ወጪየሆኑ ህገወጥ አሰራሮችን ለማካላከል፤

በአሁኑ ወቅት በሃገራችን ተግባራዊ የሚደረገው የንቅለ ተከላ ህክምና የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ባላቸው ግለሰቦች ማካከል ብቻ ማሆኑን ለሚደንገግ፤

በንቅለ ተከላ ህክምና ተሳታፊ የሚሆኑ አካላትን ከሚደበኛ ተግባርና ሃላፊነታቸው በተጨማሪ ህክምና ወስጥ ተሳታፊ በማሆናቸው የሚጠበቅባቸወን ተግባርና ሃላፊነት በዝርዝር ለማስቀመጥ፤

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 691/2003 በአንቀፅ 10 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**1. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ መመሪያ "በህይወት ባሉ ዘመዳሞች መካከል ስለሚደረግ የአካል ክፍሎች ንቅለ ተከላ ህክምና አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 344/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. <u>አውጪው አካል</u>**

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀፅ 10 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**3. <u>ትርጉም -</u>**

በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡-

1. "ንቅለ ተከላ" ማለት ከአንድ ሰው የአካል ክፍል ወስዶ ወደ ሌላ ሰው አካል መትከል ማለት ነው፡፡
2. "አካል ልገሳ" ማለት አካልን በፈቃደኝነት ለሌላ ሰው አሳልፎ ለንቅለ ተከላ አላማ መስጠት ማለት ነው፡፡
3. "ለጋሽ" ማለት ከተለጋሽ ጋር የጋብቻ ወይም የስጋ ዝምድና ያለው ሆኖ አካሉን ለተቀባይ በፍቃደኝነት የሚሰጥ ሰው ማለት ነው፡፡
4. "ተቀባይ" ማለት ከለጋሽ ጋር የጋብቻ ወይም የስጋ ዝምድና ያለው ሆኖ የለምንም ክፍያ ከለጋሽ አካል የተሰጠው ሰው ነው፡፡
5. "አካል" ማለት በዚህ መመሪያ ተፈቀዱ አካላትን ወይም የአካል ክፍሎችን የሚጠቃልል ነው፡፡
6. "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

7. “የጤና ተቋም” ማለት የጤና ማበልፀግ፣ የበሽታ ከላከል፣ ማከምና ሜልሶ ሜቋቋም ስራዎችን ወይም አገልግሎት የሚሰጥና የማሰራ የሙከናወን የመንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆነ ወይም የግል ተቋም ነው፡፡

8. “የህክምና ባለሙያ” ማለት ህሙማተኛውን በመመርመር የበሽታውን አይነት የሚለይና በመድሃኒት ወይም አካልን በመቅደድ የሚያክም የሰው ሃኪም ወይም እነዚህኑ ተግባራት እንዲያከናውን በባለስልጣኑ የተፈቀደለት የጤና ባለሙያ ነው፡፡

9. “ባለስልጣን” ማለት የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድሃኒት እና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፡፡

10. “የብሄራዊ የንቅለ ተከላ ኮሚቴ” ማለት ከልገሳ በፊት የለጋሹን ፍቃደኝነት የሚያረጋግጥ እና በለጋሽ እና በተለጋሽ መካከል የጋብቻ ወይም የስጋ ዝምድና መኖሩን በሚያጋግጥ ንቅለ ተከላውን ለሚያከናውነው ተቋም አካል ልገሳ እንዲከናወን ፍቃድ የሚሰጥ በባለ ስልጣኑ የሚቋቋም ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት የተውጣጡ አባላት ሰስብስብ ነው፡፡

11. “የንቅለ ተከላ ተቋም” ማለት በባለ ስልጣኑ ልዩ ፍቃድ የተሰጠው የንቅለ ተከላ ተግባር የሚያከናውን የጤና ተቋም ነው፡፡

12. “በምክር ላይ የተመሰረተ ፍቃድ” ማለት ንቅለ ተከላ የሚድረግ ሂደቱ፣ ተፅዕኖ ፣ ጉዳቱና ጠቀሜታውን ለጋሹ በሚረዳው ቋንቋ ወይም ምልክት ምክር ተሰጥቶት ፍቃዱን ማስጠት ነው፡፡

13. “የህክምና ደረጃ” ማለት ባለስልጣኑ ለጤና ተቋም ፍቃድ ሲሰጥ የጤና ተቋማቱ ማሟላት ያለባቸው መስፈርት ሲሆን መስፈርቱ በህግና የሙያው ስነምግባር የሚጠይቀውን ሁኔታዎች መሰረት ያደረገ ነው፡፡

14. “ዘመዳሞች” ማለት በለጋሽና በተለጋሽ መካከል የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያላቸው የተፈጥሮ ሰዎች ናቸው፡፡

በዚህ መመሪያ ወስጥ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል ፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

1. ይህ መመሪያ በህይወት ባሉ የጋብቻ እና የስጋ ዘመዳሞች መካከል የሚደረግ የአካል ልገሳን እና የንቅለ ተከላ ህክምናን በተመለከተ የሚከሄዱ ተግባሮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2. መመሪያው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ላይ ተፈፃነት የለውም፤

ሀ. አእምሮው ከሞተ ሰው የሚደረግ ንቅለ ተከላ፣

ለ. ከሞተ ሰው የሚደረግ የአካል ንቅለ ተከላ፣

ሐ. የመራቢያ አካላት ንቅለ ተከላ፣

## ክፍል ሁለት

## ስለ ለጋሽ እና በምክር ላይ የተመሰረተ ፍቃድ

## 5. ለጋሽ ስለመሆን

የሰው የአካል ክፍል በህይወት ካለ ለጋሽ ለንቅለተከላ  አላማ የሚወሰደው በለጋሽና በተለጋሽ መካከል የጋብቻ ወይም የስጋ ዝምድና ሲኖር እና በምክር እና ገለፃ ላይ የተመሰረተ ፍቃድ ከለጋሹ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

## 6. በህግ ስለሚፀና ፍቃድ

1. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 መሰረት በምክር ላይ የተመሰረተ ፍቃድ እንደተሰጠ የሚቆጠረው፡-

    ሀ. ለጋሹ ልገሳውን ለማድረግ በህግ የሚፀና ፍቃድ ማስጠት የሚችም ሲሆን፣

    ለ. ለጋሹ ፍቃዱን የሰጠው በሙሉ ፍቃደኝነት ወይም ባለመታለል ወይም ከተፅዕኖ ወጪ ወይም ሳይገደድ ወይም በማንኛውም መንገድ ጉድለት በሌለበት ሁኔታ ሲሆን፣

    ሐ. ለጋሹ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 መሰረት በቂ መረጃ ሲያገኝ፣

    መ. ለጋሹ መስማማቱን የሚገልፅ የፅሁፍ ማስረጃ ሲኖር ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ (1) (ሀ) መሰረት ህግ የሚፀና ፍቃድ መስጠበት የሚችል ሚለት

ሀ. እድሜው 18 እና ከዚያ በላይ የሆነ

ለ. የአእምሮ ጤና እክል የሌለበት ሚሆት ነው፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለጋሹ እድሜው 18 አመት ባይሞላውም በልዩ ሁኔታ በሞግዚቱ ወይም ባሳዳሪው ፍቃድ ሰጪነት የፍልቁ አጥንት(ቦን ሚሮው) ሊለግስ ይችላል፡፡

4. የለጋሹ ፍቃድ የተገኘው በሚታለል ወይም በማስገደድ ወይም በማስፈራራት ወይም የገንዘብ ጥቅም ለማስገኘት ወይም ለማግኘት ወይም በማንኛውም መንገድ ፍቃድን በህግ ፊት እንዳይፀና በሚያደርጉ በህግ በተደነገጉ ሁኔታ የተገኘ ከሆነ ፍቃዱ ጉድለት እንዳለበት ተቆጥሮ ወድቅ ይሆናል፡፡

5. ለጋሹ በማንኛውም ጊዜ ከላይ በተዘረዘረው አግባብ የሰጠውን ፍቃድ ማቋረዙን ንቅለተከላው ከመካናወኑ በፊት በፅሁፍ ወይንም በቃል ወይም በማንኛውም ሁኔታ ሊገልጽ ይችላል፡፡

7. **<u>ምክር እና ገለፃ</u>**

1. በዚህ መመሪያ መሰረት የለጋሹ ፍቃድ በምክር እና ገለፃ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ የሚቆጠረው፣

ሀ. ለጋሹ በማንኛውም ሰዓት የልገሳውን ፍቃድ ማቋረዝ እንደሚችል ሲገለፅለት፤

ለ. ለጋሹን ለንቅለተከላ ለማዘጋጀት በሰውነት ላይ የሚደረግ የህክምና ሂደት፣ የሚወሰድ መድሃኒት እና መድሃኒቱ በሰውነት ላይ የሚያመጣው ለውጥ ሲገለፅለት፤

ሐ. ልገሳው እንዴት እንደሚከናን እና ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ ሲገለፅለት

መ. ልገሳው በአጭር እና በረጅም ጊዜ ሊያስከት የሚችለው የጎንዮሽ ጉዳት ካለ ሲገለፅለት፤

ሠ. ከልገሳው በኃላ ሊመጡ የሚችሉ የአኗኗር ለውጦች እና መወሰድ ስለሚገባው ጥንቃቄ እና

ረ. ሌሎች አግባብ የሆኑ የህክምና እና ማህበራዊ ሁኔታዎች ገለፃዎች ሲደረግለት ነው፡፡

2. ማንኛውም ምክር እና ገለፃ ለጋሹ በሚዳው ቋንቋ ወይም ምልክት መደረግ አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የተዘረዘሩት ለለጋሹ የሚደረጉ ምክር እና ገለፃዎች ከልገሳው በፊት ማስጠታቸዉን የሚያመለክት ሠነድ በተቋሙ ተዘጋጅቶ እና ተረጋግጦ ለኮሚቴው መቅረብ አለበት፡፡

## ክፍል ሶስት

## ስለ ለጋሽ መረጃ እና የመረጃ ጥንቅር

### 8. መረጃ ስለ መመዝገብ

1. ይህን መመሪያ መሰረት በማድረግ በሚዘጋጅ የአሰራር ፕሮቶኮል ኮሚቴው የለጋሽ እና የተለጋሹን ሙሉ መረጃ ይመዘግባል፡፡

2. ስለለጋሹ የተሰጠው መረጃ በተገቢው ሁኔታ ሰነድ ተደርጎ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

3. የህክምና ተቋማት የአካል ንቅለተከላ ያደረጉ ሰዎችን ያጋጠሟቸዉን የጎንዮሽ ጉዳት ወይም ማንኛውም ውጤት መዝግበው ማስቀመጥ ይገባቸዋል፡፡

4. የተመዘገቡትን መረጃዎች በየጊዜው ለባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ሚስጥራዊነትን በጠበቀ ሁኔታ ማሳወቅ ይገባቸዋል፡፡

5. የአካል ንቅለተከላን ደህንነት እና ጥራት ለሚረጋገጥ በአካል ንቅለተከላ ላይ የተሰማራው የህክምና ቡድን አስፈላጊ የሆኑ የለጋሽ መረጃዎችን የማሰባሰብ እና በለጋሹ ላይ ያለዉን ውጤት ለለጋሹ በአግባቡ መግለፅ አለበት፡፡

### 9. ስለመረጃ ይዘት

1. በአካል ንቅለተከላ ላይ የተሰማሩ የህክምና ባለሞያ ከንቅለተከላ በፊት ንቅለተከላው የሚከሄድበትን ተቋም፣ የአካል እና የለጋሽ ማለያ ፣ የለጋሹ የደም አይነት ፣ ፆታ፣ የትወልድ ቀን እና ዓመተ ምህረት፣ ክብደት፣ ቁመት፣ የአደንዛዥ እፅ ተጠቃሚነት፣ ተላላፊ በሽታዎችን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ማስረታዊ የግል መረጃዎችን በማሰባሰብ የአካልና ለጋሽ ማለያ መረጃዎችን ማሰባሰብ ይኖርበታል፡፡

2. እንደ ሚጀው ማንት እና አስፈላጊነት የላብራቶሪ ሚጀችን እና ሌሎች አስፈላጊ ሚጀዎችን ማሰብሰብ አለባቸው፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የተጠቀሱት እንጉዳዩ አግባብነት ለተለጋም ያገለግላሉ፡፡

## 10. ሚጀን ስለማግኘት

1. የለጋሽን እና የተለጋሽን የወደፊት ጤንነት በአግባቡ ለማጠበቅ ሲባል የአካል ንቅለተከላ የሚካሄድ ተቋምና ባለሞያ የለጋሽ እና የተለጋሽን የጤና እና ሌሎች አስፈላጊ ሚጀዎችን ወደኃላ ተሚሉሶ ለማግኘት እንዲቻል ሚጀ ሞዝ አለባቸው፡፡

2. ንቅለተከላ የሚከሄደበት ተቋም ለጋሽ እና ተለጋሽን ወደኃላ ተሚሉሶ ለማግኘት እንዲቻል ለጋሽ እና ተለጋሽ የሚኖዩበትን እና የሚገኙበትን ስርዓት የማዘርጋት ሃላፊነት አለበት፡፡በንቅለተከላ ህክምና ምክንያት የሚገኝ ማንኛውም የህክምና ሚጀ ምስጢራዊ በሆነ መንገድ መቀመጥ እና ህግ በሚፈቅደው ሁኔታ ማጋለጥ የለበትም፡፡

3. ባለስልጣኑ ወይም በንቅለተከላ ጊዜ የሚተፍ ማንኛውም አካል ሚጀን ወደኃላ ተሚሉሶ ማግኘት እንዲቻል በሂደት የተገኘን ሚጀ በአግባቡ ማከቀመጥ ይኖርበታል፡፡

4. ሚጀን ወደኃላ ተሚሉሶ ማግኘት እንዲቻል በዚህ መመሪያ መሰረት የተሰበሰበ ሚጀ እስከ ለ30 (ሰላሳ) አመታት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አራት

## የአካል ክፍሎች ንቅለ ተከላ

### 11. የአካል ክፍሎች ጥበቃ፣ ክብር እና ደህንነት

1. ማንኛውም የአካል ክፍል እና ህብረ ህዋስ ለተቀባዩ ሊሰጥ የሚችለው ደህንነቱ፣ ጥራቱ እና ተስማሚነቱ ሲረጋገጥ ነው፤

2. የአካል ክፍሎች ደህንነት እና ጥራትን በተመለከተ ባለስልጣኑ የአሰራር መስፈርት ሊያወጣ ይችላል፤

3. የአካል ክፍሎች እና ህብረ ህዋስ ህክምና በመስጠት ላይ የሚተፍ ባለሞያ እና ተቋም የአካሉን ጥራት እና ደህንነት ለማስጠበቅ ተገቢውን ደረጃ እና መስፈርት መከተል አለበት፡፡

4. አካል ክፍል ለጋሽ የሚሚጠው ይህን መሜያ ማስረት በሜድረግ የሚዘጋጅ ዝርዝር ፕሮቶኮል ፣ የጤንነት ሁኔታውን እና የህክምና ታሪኩን ማስረት በሜድረግ መሆን ይኖርበታል፡፡ በዚህ አይነት ሚዝና ንቅለ ተከላው በጤንነታቸው ላይ ጉዳት የሚያደርስባቸውን ሰዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ ሚፈቀድ የለበትም፡፡

5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 እንደተጠበቀ ሆኖ የተጠቀሰው የጤንነት ጉዳት ንቅለተከላውን ለሜድረግ የሚያስችል መሆን አለመሆኑን የአገልግሎት ሰጭ ተቋሙ የህክምና ቦርድ የሚወሰነው ይሆናል፡፡

6. የለጋሹን የአካል ጉዳትና የስነልቦና ተፅእኖ ለመቀነስ የአካል ክፍል ከመወሰዱ በፊት አግበብ ያለው የህክምና ምርመራና እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

## 12. ከንቅለተከላ በኃላ የሚደረግ እንክብካቤ

ሀ. ከንቅለተከላው በኃላ ለለጋሽም ሆነ ለተቀባይ የሚደረገው አግባብ ያለው የህክምና እንክብካቤ ንቅለተከላውን የሰራው ተቋም ማከናወን አለበት፡፡

ለ. የህክምና ቅብብሎሽ ስርዓቱ በሚፈቅደው ማስረት የድህረ እቅለተከላ ህክምና በሌላ ተቋም ሊደረግ ይችላል፡፡

ሐ. ንቅለተከላ ከማከናወኑ አስቀድሞ ለህክምና የሚያስፈልገው አጠቃላይ ወጪ በህክምና ተቋሙ ተሰልቶ ለተለጋሽ ማለፅ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ተግባርና ሃላፊነት

## 13. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተግባርና ሃላፊነት

ሀ. ከተለያዩ ተቋማት የተወጣጡ የብሄራዊ የንቅለተከላ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፤

ለ. የኮሚቴውን ስራ በየጊዜው ይቆጣጠራል፣ ሪፖርቶችን ይገመግማል፣ በሚቀርብለት ሪፖርት ማስረት ማስተካከያ ይሰጣል፤

ሐ. ኮሚቴው ለስራው የሚያስፈልጉትን ማንኛውም ግብአቶች ከባለስልጣኑ ጋር በጋራ በመሆን እንዲሟሉለት ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## 14. <u>የባለስልጣኑ ተግባርና ሃላፊነት</u>

ሀ. የአካል ንቅለተከላ ለሚያካሄዱ የጤና ተቀዋማት እና ባለሙያዎች ልዩ ፍቃድ ይሰጣል፤

ለ. የአካል ንቅለተከላ ለሚያካሄዱ የጤና ተቋማት መሟላት የሚገባቸውን መስፈርት ያወጣል፤

ሐ. የአካል ንቅለተከላ ለማካሄድ ፍቃድ የተሰጣቸውን የጤና ተቋማት ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ በየአመቱ ፍቃድ ያድሳል፣ ከደረጃቸው ዝቅ ያሉትን ፍቃዳቸውን ያሰርዛል፤

መ. የአካል ንቅለተከላ የሚያካሄዱ የጤና ተቋማት የሚያገኛቸውን መረጃዎች በሚስጥር ይጠብቃል፤

ሠ. የአካል ንቅለተከላ የሚያካሄዱ የጤና ተቋማት ሪፖርት በየጊዜው እየተከታተለ ይቀበላል፤ በሪፖርቱ ላይ ግብረ መልስ እና የስራ ማስተካከያ ትዕዛዝ ይሰጣል፤

ረ. በዚህ መመሪያ መሰረት የሚቋቋመውን ኮሚቴ ለስራው የሚያስፈልጉትን ማንኛውም ግብአቶች ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በጋራ በመሆን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## 15. <u>የጤና ተቋም ተግባርና ሃላፊነት</u>

በዚህ መመሪያ መሰረት የንቅለተከላ የሚያከናውን ማንኛውም የጤና ተቋም ፡-

ሀ. የአካል ንቅለተከላ ለማካሄድ የሚችለው ከባለስልጣኑ ልዩ ፍቃድ ሲሰጠው ብቻ ነው፤

ለ. ፍቃድ ባገኘበት መስፈርት መሰረት ስራን ያከናውናል፣ፍቃዱን በየአመቱ ያድሳል፣ፍቃዱን ለሌላ ሶስተኛ ወገን ወይም ተቋም ማስተላለፍ አይችልም፤

ሐ. የንቅለተከላን አስፈላጊነት በተቋሙ የህክምና ቦርድ ያስወስናል፤

መ. ባለስልጣኑ በወሰነው የጊዜ ገደብ ሪፖርት ያደርጋል፣ በሪፖርቱ መሰረት የተሰጡትን ግብረመልሶች እና ማስተካከያዎች ተግባራዊ ያደርጋል፤ባለስልጣኑ የጠየቀውን ማናቸውንም መረጃ ይሰጣል፤

ሠ. የለጋሽን በምክር ላይ የተመሰረተ ፍቃድ እና የዝምድና መረጃዎችን አደራጅቶ ለንቅለተከላ ኮሚቴው ያቀርባል፤

ረ. የለጋሽንና የተለጋሽን መረጃ በሚስጥር ይጠብቃል፤የጤንነትን ሁኔታ በአግባቡ ይመረምራል፤ ከልገሳ በኃላ ወይም በልገሳው ጊዜ በጤና ላይ ሊደርስ የሚችል መታወክ አለመኖሩ በምርመራ ያረጋግጣል፤

ሰ. ከኮሚቴው ፍቃድ ሲያገኝ ለንቅለተከላ የሚረዳ ቅድመ ምርመራ እና ህክምና ያካሄዳል፤

ሸ. ለንቅለተከላ ለሚወሰደው የለጋሹ አካል ከተለጋሹ ጋር የሚስማማ መሆኑን ያረጋግጣል፤

በ. ንቅለተከላ ከመካሄዱ በፊት ለጋሹ በማንኛውም ሰዓት ፍቃደኝነቱን የማንሳት መብቱን ያከብራል፤

ቀ. ለጋሹ ለንቅለተከላ ፍቃደኛ እንዲሆን ወይም ፍቃደኝነቱን እንዲያነሳ ለማድረግ የማባበል፣ የሙከለል፣ የማስማት ስራዎች እንዳይሰሩ የበኩሉን ጥረት ያደርጋል፤

ተ. ንቅለተከላውን የሚያካሄደው ተቋም በዚህ መመሪያ መሰረት ከንቅለ ተከላ በፊት የአካል እና ለጋሽ ማለያ ስራ መደረጉን፣በዚሁ መሰረት ሚዛኝ ማያዙን እና አካሉ ከወጣ በኋላ በአግባቡ ለማጠበቅ ቅድመ ሁኔታዎች እንደተሟሉ ሚጋገጥ አለበት፣

ቸ. ለአካል ንቅለተከላ የሚውሉ ማንኛውም የህክምና መሳሪያዎች እና ተያያዥ ማልገያዎች አግባብ ያለውን የደህንነት እና ጥራት ደረጃ ማሟላታቸውን ሚጋገጥ አለበት፡፡

ኘ. ለንቅለተከላው አስፈላጊ የሆኑ የህክምና ዝርዝር ፕሮቶኮል ያወጣል፡፡

16. <u>የጤና ባለሙያዎች ሃላፊነት</u>

ሀ. የአካል ለጋሽ ሚጣ ወይም ምዝናን ጨምሮ አካል በሚጥበት እና ጥበቃ በሚከሄድበት ተቋም የሚከሄድ ማንኛውም የህልምና ተግባር መካሄድ ያለበት አግባብ ባለው እና በባለስልጣኑ የተፈቀደለት የህክምና ባለሙያ ብቻ ነው፡፡ በማንኛውም አካል ንቅለተከላ እስከ አካል ማስወገድ ድረስ የሚሳተፍ ማንኛውም የጤና ባለሙያ ብቃት ያለው እና ተፈላጊውን ስልጠና ያገኘ መሆን አለበት፡፡

ለ. የጤና ባለሙያ የአካል ልገሳው በጤናቸው ላይ ጉዳት የሚያደርስባቸው ሰዎች ለልገሳ ተሳታፊ እንዲሆኑ መፍቀድ የለበትም፡፡

ሐ. የአካል ንቅለተከላ ወስጥ የሚሳተፍ ማንኛውም የህክምና ባለሙያ ወይም የጤና ተቋም የአካሉን ጥራት እና ደህንነት ለማስጠበቅ ተገቢውን መስፈርትና ፕሮቶኮል መከተል አለበት፡፡

17. <u>የብሄራዊ አካል ንቅለተከላ ኮሚቴ ተግባር፣ኃላፊነትና አሰራር</u>

በዚህ መመሪያ መሰረት የንቅለተከላ ከመካሄዱ በፊት የለጋሹን ፍቃደኝነት እንዲሁም በለጋሽና በተለጋሽ መካከል የጋብቻ ወይም የስጋ ዝምድና መኖሩን የሚያረጋግጥ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ የሆነ ኮሚቴ የተቋቋመ ሲሆን ኮሚቴው፡-

1. ለንቅለተከላ ህክምና የቀረቡትን ለጋሽ እና ተለጋሽ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 8 በተሰጠው ዝርዝር መሰረት ዝምድና ያጣራል፤
2. የለጋሽን ፍቃደኝነት እና ከተለጋሹ ጋር ከአካል ንቅለተከላው ጋር የተያያዘ የጥቅምና የንግድ ግንኙነት እንደሌለው ያረጋግጣል፤
3. ለጋሽ እና ተለጋሹ ስልጣን ካለው አካል የሚያቀርቡትን ሚዛኛዎችን ይመረምራል፤
4. ኮሚቴው 8 (ስምንት) ያህል አባላት ይኖሩታል፡፡
   ሀ. የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተወካይ. ሰብሳቢ
   ለ. በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሜዲካል አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ..............ፀሃፊ
   ሐ. በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የህግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት...አባል
   መ. የሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካይ.....አባል

ሠ. የሴቶችና ህፃናት ሚኒስቴር ተወካይ.........አባል

ረ. የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ተወካይ.......አባል

ሰ. የኢትዮጵያ የሕግ ባለሞያ ሴቶች ማህበር ተወካይ....አባል

ሸ. የአዲስ አበባ ጠፍ ቢሮ ተወካይ.....አባል

ቀ. የሰነዶች ምዝገባና ሚኒጋገጫ ጽ/ቤት ተወካይ...አባል

በ. የኢትዮጵያ የእምነት ተቋማት ህብረት ተወካይ...አባል

5. ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ኮሚቴው ስብሰባውን ያካሂዳል፤

6. የኮሚቴው ውሳኔ በድምፅ ብልጫ ሲሆን እኩል ድምፅ ሲገኝ የኮሚቴው ሰብሳቢው ያለበት ወገን አሸናፊ ይሆናል፤

7. የኮሚቴው ማስብሰቢያ ጊዜ እና ቦታ በኮሚቴው ዝርዝር የአሰራር ቢጋር ይወሰናል፤

8. ኮሚቴው ዝርዝር የአሰራር መመሪያ በማዘጋጀት ለሚኒስት አቅርቦ ያፀድቃል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**18. የተከለከሉ ተግባራት**

ይህን መመሪያ ማስረት በማድረግ፡-

ሀ. በእርግዝና ወቅት ካለች ሴት የአካል ክፍል መውሰድ፣

ለ. በእስር ላይ ካሉ ሰዎች የአካል ክፍል መውሰድ፣

ከአእምሮ ህሙማን የአካል ክፍል መውሰድ አይቻልም፡፡

**19. የህግ ተጠያቂነት**

1. ማንኛውም ንቅለተከላ የሚያከናውን የህክምና ባለሞያ እና ተቋም ንቅለተከላ ሲያከናውን የሞያውን የስለምግባር ደንብ እና አግባብ ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች ማክበር አለበት፡፡

2. በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች በተቃረነ ሜኩ ንቅለተከላ የሚያካሄድ የህክምና ባለሞያ ወይም ተቋም የወንጀልና የፍትሐብሔር ተጠያቂነቱ እንደተጠበቁ ሆነው

ሀ. ባለስልጣኑ እንደነገሩ ሁኔታና እንደ ጉዳዩ ክብደት ከፅሁፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ፍቃድ ስረዛ ሊደርስ የሚችል እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

ለ. ተጎጂው አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ በሚድረግ ካሳ ሊያስከፍል ይችላል፡፡

ሐ. የካሳ አከፋፈልን በተመለከተአግባብ የሆነ የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

20. **የመተባበር ግዴታ**

ይህ መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን የሚመለከታቸው አካላትና የጤና ተቋማት የመተግበር ግዴታ አለባቸው፡፡

21. **የቅሬታ አቀራረብ**

ሀ. ከመኖ ስለምግባር ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች ለባለስልጣኑ መቅረብ አለባቸው፡፡

ለ. በብሄራዊ አካል ንቅለተከላ ኮሚቴ አሰራርና ወሳኔዎች ዙሪያ ያሉ ቅሬታዎች ለሚኒስቴሩ መቅረብ ይችላሉ፡፡

22. **መመሪያውን ስለሚሻሻልበት ሁኔታ**

ሚኒስቴሩ መመሪያውን ተግባራዊ ሲያደርግ ክፍተቶች ሲያጋጥሙ መመሪያውን ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

23. **ተፈፃሚነት ስለሚይኖራቸው ህጎች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያና ልማዳዊ አሰራር ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

24. **መመሪያው ተፈፃሚ ስለሚሆንበት**

ይህ መመሪያ ከጥር ......ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ከሰተብርሃን አድሚኩ(ዶ/ር)

የጤና ጥበቃ ሚኒስትር